# Übersetzung der Dialoge

# የውይይቶች ትርጉም

## Lektion 1

### ማነሽ አንቺ?

በመጀመሪያው ምዕራፍ ጀርመንኛን ለመረዳት የሚያግዘው አንድ ዘዴ ይደገማል። ከዚሁ በተጨማሪ የኮርሱን ዋና ዋና ባለሚናዎች በደጋሚ እናስተዋውቃለን።

| | |
|---|---|
| Andreas Schäfer: | የጋዜጠኝነት ሙያ ተማሪ ነው። በትርፍ ጊዜው ኮርሱ በሚካሄድበት በአኹኑ ሆቴል አውሮፓ በእንግዳ ተቀባይነት ይሰራል |
| Ex: | አንዲት አነስት የፈጠራ ምስል ናት |
| Hanna: | ሆቴል አውሮፓ ውስጥ ክፍል አጽጂ ናት |
| Dr. Thürmann: | የሆቴል አውሮፓ ቋሚ እንግዳ ነው |

የሰዎቹ ማንነት የሚደገመው በአንድ አውጣጪኝ (እንቆቅልሽ) አማካይነት ነው። ይሄውም በቋንቋ ኮርሳችን ክፍል 1 ውስጥ የተፈጸሙ ድርጊቶችን ብቻ ነው የሚጠቀልለው። እርግጥ ከአንድ ሁኔታ በስተቀር! አንዲት ሴት የሆነ ቲያትር ቤት፣ ማለት “አቫንቲ ቲያትርቤት”ን ትፈልጋለች።

| | |
|---|---|
| ሴትዮዋ | ይቅርታ ያድርጉልኝ፣ አቫንቲ ቲያትር ቤት የት ነው? |
| ሰውዬው | አቫንቲ ቲያትር? አቫንቲ ቲያትር? ህም-አላውቀውም |

## Lektion 2

### ምን ላደርግልዎት እችላለሁ?

የሚከተሉት ሶስት ድርጊቶች የሚፈጸሙት በሆቴል አውሮፓ እንግዳ መቀበያ ስፍራ ነው። በመጀመሪያው ድርጊት አንድ ወጣት ሰው ስልክ መደወል ይችል እንደሆን ይጠይቃል።

| | |
|---|---|
| ሰውዬው | ጤናይስጥልኝ፣ እዚህ ስልክ ይኖራል? |
| አንድሬያስ | እንዴታ! |
| ሰውዬው | መደወል እችላለሁ? |
| አንድሬያስ | በደስታ! ስልኩ እዚህ ነው ያለው፣ ይሄው! |
| ሰውዬው | አመሰግናለሁ! |
| | (ሰውዬው ቁጥሩን እያጉረመረመ ይደውላል) |
| | ሁለት-አምስት-አንድ-ዘጠኝ-ዜሮ-አራት |
| | (ስልኩ ይጮህና ተቀባይዋ ታነሳዋለች) |
| ሴትዮዋ | ቤከር |
| ሰውዬው | ሽሚት፣ ጤናይስጥልኝ ወሮ/ቤከር |

በሁለተኛው ድርጊት አንድሬያስ ለአንዲት ጠና ያሉ ሴት ወደ ባቡር ጣቢያ የሚወስደውን መንገድ ይገልጻል።

| | |
|---|---|
| አንድሬያስ | ጤናይስጥልኝ |
| አንጋፋዋ ሴት | ይቅርታ ያድርጉልኝ፣ ሊረዱኝ ይችላሉ? |
| አንድሬያስ | በደስታ |
| አንጋፋዋ ሴት | ያውቃሉ፣ እኔ እዚህ ባዕድ ነኝ |
| አንድሬያስ | እና እንዴት ነው ልረዳዎት የምችለው? |
| አንጋፋዋ ሴት | ባቡር ጣቢያውን ነው የምፈልገው |
| አንድሬያስ | ባቡር ጣቢያው ከዚህ በጣም ቅርብ ነው |
| አንጋፋዋ ሴት | እግዜር ምስጋና ይግባው! |
| አንድሬያስ | በጣም ቀላል ነው። በመጀመሪያ ወደ ቀኝ ይሄዳሉ |
| አንጋፋዋ ሴት | (በመድገም) በመጀመሪያ ወደ ቀኝ |
| አንድሬያስ | እና ከዚያም ሁለተኛውን መንገድ |
| አንጋፋዋ ሴት | ሁለተኛውን መንገድ |
| አንድሬያስ | እንደገና ወደ ቀኝ |
| አንጋፋዋ ሴት | እንደገና ወደ ቀኝ |
| ኢክስ | በመጀመሪያ ቀኝ፣ ከዚያም ሁለተኛውን መንገድ፣ እንደገና ወደ ቀኝ |
| አንጋፋዋ ሴት | በጣም አመሰግናለሁ |
| ኢክስ | ምንም አይደል! |

በሶስተኛው ድርጊት ኢክስ ጊደኛች...  ትፈልጋለች።

| | |
|---|---|
| ኢክስ | ይቅርታ ያድርጉልኝ፣ ሊረዱኝ ይችላሉ? |
| አንድሬያስ | በደስታ፣ ክብርትነትዎ |
| ኢክስ | ያውቃሉ፣ እኔ እዚህ ባዕድ ነኝ |
| አንድሬያስ | ምን ላደርግልዎት እችላለሁ? |
| ኢክስ | ጊደኛች...  እየፈለግሁ ነው |
| አንድሬያስ | አሃ-<br>በመጀመሪያ ወደ ግራ፣ ከዚያም ወደ ቀኝ፣ ከዚያም እንደገና ወደ ግራ፣<br>ከዚያም ያለማቋረጥ በቀጥታ ወደፊት፣ ቀጥታ፣ ቀጥታ... |

## Lektion 3

አማካይ ስፍራ ላይ ነው የሚገኘው

| | |
|---|---|
| አንድሬያስ | ጤናይስጥልኝ፣ እንዴት አመሻችሁ |
| ሴትዮዋ | እንዴት አመሹ፣ አንድ ክፍል እንፈልጋለን |
| አንድሬያስ | ኦህ-ግን በጣም አዝናለሁ። የቀረ ነጻ ክፍል የለንም |
| ሰውዬው | ጉድ ነው! ይሄ ሶስተኛው ሆቴል መሆኑ ነው! |
| አንድሬያስ | ወደ ካርልከ ሆቴል ለመደወል ዝግጁ ነኝ፣ አማካይ ስፍራ ላይ ነው |
| ሴትዮዋ | አውቃለሁ። እዚያም ነበርን፣ ግን ጩኸት ይበዛዋል |
| አንድሬያስ | ሆቴል ኩዌለስ?  ከዚያም ደርሰው ነበር? |

| | |
|---|---|
| ሴትየዋ | አዎን፣ እዚያ በጣም ውድ ነው |
| ሰውዬው | ሁልጊዜ የምትረኪ አይደለሽም! |
| ኢክስ | የማትረኪ፣ የማትረኪ፣ የማትረኪ... |
| አንድሬያስ | ዝም በይ እስቲ! |

አንድሬያስ ያቀረባቸው ሁለት ሃሣቦቹ የባልና ሚስቱን ሰዎች ተቀባይነት ባለማግኘታቸው ወደ አንድ "ፔንዚዮን" (መለስተኛ ሆቴል) ለመደወል ዝግጁ እንደሆነ ይገልጻል።

| | |
|---|---|
| አንድሬያስ | ወደ አንድ ፔንዚዮን፣ "ፔንዚዮን ኮኒግ" መደወልም እችላለሁ |
| ሴትየዋ | እና እሷስ እንዴት ናት? |
| አንድሬያስ | በጣም ረጋ ያለች - ግን አማካይ አይደለችም |
| ሰውዬው | የራሱ ጉዳይ! እባክዎ ከዚያ ይደውሉ! |
| ሴትየዋ | ቆይ አንዴ! እንዴት ነው ከዚያ የምንደርሰው? |
| አንድሬያስ | ታክሲ ላዝልዎት እችላለሁ። ቁጥር 40 አውቶቡስም ወደዚያው ይሄዳል። ከዚያው አጠገብ ነው የሚያቆመው |
| ሴትየዋ | ይሁን መልካም |
| አንድሬያስ | እንግዲያው አሁን ወደዚያ እደውላለሁ |

## Lektion 4
### የማይቻል!

አንድሬያስ የሆቴል አውሮፓ ስራውን ጨርሶ ወደ ቤቱ ለመሄድ እየተነሳ ነው። በዚሁ ወቅት የሆቴሉ ሃላፊ ወሮ/በርገር ብቅ ትላለች። ወሮ/በርገር አንድሬያስ እርካታ እንደማይታይበት ትነግረዋለች።

| | |
|---|---|
| ወሮ/በርገር | ሄላው፣ አቶ ሺፈር |
| አንድሬያስ | እንዴት አመሹ፣ ወሮ/በርገር |
| ወሮ/በርገር | ምነው፣ ችግር ገጥሞዎት ነበር እንዴ? |
| አንድሬያስ | የለም፣ ለምን? |
| ወሮ/በርገር | ያን ያህል የረኩ አይመስሉም |
| አንድሬያስ | ማን? እኔ? |
| ወሮ/በርገር | አዎን፣ እርስዎ! ታዲያ ሌላ ማን? |
| ኢክስ | እኔ አይደለሁም! |
| ወሮ/በርገር | በሉ፣ አንቱ በሆድ ተናጋሪ፣ ያውሩ እስቲ! |

አንድሬያስ ስለ ባልና ሚስቱ ያወራል። ወሮ/በርገር ደግሞ "ደምበኛ ሁሉጊዜም ንጉስ" ሆኖ መታየት እንዳለበት ታስታውሰዋለች።

| | |
|---|---|
| አንድሬያስ | ደህና፣ ዛሬ አንድ ባልና ሚስት እዚህ ነበሩ። እርሱ ደስተኛ አልነበረም፣ እርሷም የረካች አልነበረችም |
| ኢክስ | የማይቻል! ሁለቱም የማይቻሉ! |

ወሮ/በርገር ይህና፣ ግን ስለ እንግዶች እንዲህ ማውራት አይችሉም!
ትህትና የጎደለው ነገር ነው!

አንድሬያስ ዕውነት አለዎት! ነይ ኤክስ፣ ወደ ቤት እንሂድ!

ወሮ/በርገር አህ - ድምጽዎ ስም አላት እንዴ?

ኤክስ በዚህም በዚያም!

ወሮ/በርገር መልካም! ግን ያውቃሉ፣ ደምበኛ ንጉስ መሆኑን

ኤክስ ንጉሱ እኔ ነኝ

አንድሬያስ የለም፣ አንቺ ንግስቲቱ ነሽ!

ስርጭቱ ሲያበቃ ኤክስ እንደሚከተለው ትሰናበታለች።

ኤክስ አድማጪ ንግስት ናት!

## Lektion 5

### አውቶቡስ የደስ ደስ ሊኖረው አይችልም

ኤክስና አንድሬያስ ከአንድሬያስ ቤት ናቸው። ኤክስ አንድሬያስ አንድ ጨዋታ አብሯት እንዲጫወት ታግባባዋለች።

ኤክስ አንድሬያስ፣ አንድ ጨዋታ እንጫወት?

አንድሬያስ ኦህ ኤክስ፣ እኔ በጣም ደክሞኛል

ኤክስ ግን እኮ በጣም ቀላል ነው!

አንድሬያስ ይሁን መልካም

በመጀመሪያው እንቆቅልሽ ጨዋታ *er*- "እርሱ" ሲባል ማንን ለማለት እንደሆነ አንድሬያስ ማውጣጣት ይኖርበታል።

ኤክስ በል አውጣጣ! እርሱ ሃኪም ነው

አንድሬያስ ማን?

ኤክስ እርሱ!

አንድሬያስ አንድ ሰው!

ኤክስ ትክክል!

በሁለተኛው ጨዋታ አንድሬያስ ማን "የደስ ደስ" ያለው ሊሆን እንደሚችል ማወቅ ይኖርበታል።

ኤክስ በል አውጣጣ! እርሱ የደስ ደስ ያለው ነው

አንድሬያስ ቁጥር 40 አውቶቡስ

ኤክስ ስህተት! አውቶቡስ የደስ ደስ ያለው ሊሆን አይችልም

አንድሬያስ ኦኬይ፣ ኦኬይ -አንድ ሰው

ኤክስ ትክክል!

አንድሬያስ በሶስተኛው አውጣጪኝ ማወቅ ያለበት ማን "ሽክ"ያለ እንደሆነ ነው።

| | |
|---|---|
| ኤክስ | በል አውጣጣ! እርሷ ሽክ ያለች ናት |
| አንድሬያስ | እንጂት ሴት |
| ኤክስ | ስህተት! |
| አንድሬያስ | ለምን? አንድ ሴት እኮ ሽክ ያለች ልትሆን ትችላለች |
| ኤክስ | አዎን፣ ግን ማውጣጣቱን ቀጥል! |
| አንድሬያስ | አንድ ጠርሙስ |
| ኤክስ | የለም በእውነቱ! |
| አንድሬያስ | ምናልባት - እንጂት ፈረንሳዊት? |
| ኤክስ | ትክክል! |

በአራተኛው ጨዋታ አንድሬያስ "ስሜትን የሚስብ" ነገር ምን ሊሆን እንደሚችል ማወቅ ይኖርበታል።

| | |
|---|---|
| ኤክስ | በል አውጣጣ! ስሜትን የሚስብ ነው |
| አንድሬያስ | አንድ ጨዋታ |
| ኤክስ | ስህተት! |
| አንድሬያስ | አንድ መጽሐፍ |
| ኤክስ | ስህተት! |
| አንድሬያስ | ለምን? አንድ መጽሐፍ እኮ የሚስብ ሊሆን ይችላል |
| ኤክስ | አዎን፣ ግን እኔ ሌላ ነገር ማለቴ ነው |
| አንድሬያስ | አንድ ባልና ሚስት |
| ኤክስ | ስህተት! |
| አንድሬያስ | እንግዲያው አላውቀውም! |
| ኤክስ | አንድ ሆቴል |
| አንድሬያስ | የለም! አንድ ሆቴል የሚስብ ሊሆን አይችልም |
| ኤክስ | እንዴታ! |
| አንድሬያስ | የለም! ሆቴል ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ሊስቡ ይችላሉ |
| ኤክስ | ሆቴልም! |
| አንድሬያስ | የለም! አሁን የኔ ተራ ነው! |

በመጨረሻው ጨዋታ ማውጣጣቱ የኤክስ ፈንታ ነው። ታዲያ የሚፈለገው ሰው እርሷ ራሷ መሆኗን አትገነዘብም።

| | |
|---|---|
| አንድሬያስ | በይ አውጣጪ! እርሱ ትህትና የጎደለው ነው |
| ኤክስ | አላውቀውም |
| አንድሬያስ | ጉጉተኛ ነው |
| ኤክስ | አላውቀውም |
| አንድሬያስ | አይታይም |
| ኤክስ | አላውቀውም |

አንድሬያስ	የምትታይ አይደለችም
ኤክስ	ምንድነው ነገሩ፣ “እርሱ” ወይስ “እርሷ”?
አንድሬያስ	የምጠይቅሽ፣ “እርሱ” ወይም “እርሷ” ወይም “ነገሩ” የማይታይ ነው?
ኤክስ	ይህን አላውቅም
አንድሬያስ	አንድ ምስል ነሽ ወይስ ጠንቋይ?
ኤክስ	እኔ እኔ ነኝ

## Lektion 6

### ምናልባት ዕርዳታ ትፈልግ ይሆን?

ሃና ከክፍል 15 የሚወጣ ጮክ ያለ ድምጽ በመስማቷ በዚያ የሚኖረው ማን እንደሆነ ለማወቅ ትፈልጋለች። ሃና በዚሁ ወቅት ሲትዮዋ ብቻዋን መሆኗን ተገንዝባለች።

ሃና	ሄላው አንድሬያስ!
አንድሬያስ	ሰላም ሃና። እንዴነሽ?
ሃና	ይህና! (ዝቅ ባለ ድምጽ) ንገረኝ እስቲ፣ ክፍል 15 ውስጥ ያለው ማነው?
አንድሬያስ	ወሮ/ቪመር - ለምን?
ሃና	ሁልጊዜ ጮክ ብላ ነው የምትናገረው - ግን ብቻዋን ናት
	ና -እስቲ ስማ!

ሃናና አንድሬያስ ከወሮ/ቪመር ደጃፍ ጠጋ ብለው ያደምጣሉ። የሆቴሉ ሃላፊ ወሮ/በርገርም ትጨመራለች። ወሮ/ቪመር ተዋናይ ስትሆን አንድ ሚና እየተለማመደች ነው።

ወሮ/ቪመር	የለም!:	የለም
	እዚያ!:	የለም
	እዚህ!:	የለም!
	ወደላይ:	የለም!
	ወደዚያ:	የለም። የለም። የለም
	የዕርዳታ ያለህ?	አዎን!
	የዕርዳታ ያለህ?	አዎን!
	የዕርዳታ ያለህ?	አዎን!
	(ጸጥታ፣ ጋብታ)
ሃና	ምናልባት ዕርዳታ ትፈልግ ይሆን?
አንድሬያስ	ለምን እርሷን አትጠይቂያትም!
ሃና	ግን እኮ አባካችሁ አትረብሹ! የሚል ሰሌዳ ተሰቅሏል
	(ወሮ/በርገር ወደዚያው ትመጣለች)
ወሮ/በርገር	እንግዲያማ እርስዎም አይረብሹ!
ሃና	ግን ምን እየሆነ ነው?
ወሮ/በርገር	ወሮ/ቪመር ተዋናይ ናት

ሃና	አሃ! እንዲህ ከሆነማ ሁሉም ግልጽ ነው!
እና መቼ ነው ክፍሉን ማጽዳት የምችለው?

አንድሬያስ ወደ እንግዳ መቀበያው ይመለሳል። እዚያም አንድ ከወሮ/ቢ.መር ጋር ቀጠሮ ያለው ሰው ይጠብቀዋል።

አንድሬያስ	ጤናይስጥልኝ! ልረዳዎት እችላለሁ?
ሰውዬው	ከወሮ/ቢ.መር ጋር ቀጠሮ አለኝ
አንድሬያስ	እህ፣ ክፍል 15 ውስጥ ያለችው ወሮ/ቢ.መር፣ አሁኑኑ እደውልላታለሁ
(አንድሬያስ ይደውላል፣ ግን ስልኩን ማንም አያነሳም)
አዝናለሁ! ስልኩን አታነሳም
ሰውዬው	ሊገባኝ አይችልም
አንድሬያስ	አሁን ወሮ/ቢ.መርን ለማወክ አልችልም። ምናልባት መጠበቅ ይፈልጋሉ?
ሰውዬው	አላውቅም፣ አላውቅም... እህ - ዘግየት ብዬ እንደምደውል
ለወሮ/ቢ.መር ይንገሩልኝ

## Lektion 7
### አውሮፕላኔ የሚሄደው በዘጠኝ ሰዓት ነው

አንድ ጥቂት የተደናገጠ እንግዳ በሚቀጥለው ዕለት ማለዳ ኮሎኝ አየር ጣቢያ የሚያደርስ ታክሲ እንዲታዘዝለት ይፈልጋል። አንድሬያስም ታክሲው ለስንት ሰዓት መታዘዝ እንዳለበት ይጠይቃል።

ሰውዬው	ኦህ - ለመሆኑ እዚህ ማጤስ ይቻላል?
አንድሬያስ	በእርግጥ ማጤስ ይችላሉ። ይሄው መተርኮሻ፣
ምን ላድርግልዎት?
ሰውዬው	እባክዎ ታክሲ ይዘዙልኝ። ለነገ ጧት
አንድሬያስ	በደስታ፣ እና ለስንት ሰዓት?
ሰውዬው	እንግዲህ አውሮፕላኔ የሚበረው በዘጠኝ ሰዓት ነው
ታክሲው (መንገዱ) ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል?
አንድሬያስ	በግምት አንድ ሰዓት
ሰውዬው	(ከራሱ እየተነጋገረ ጊዜውን ያሰላል)
አሃ - አንድ ሰዓት፣ በስምንት ተኩል እዚያ ለመድረስ እፈልጋለሁ፣
አንድ ሰዓት ጉዞ፣ ስለዚህም ሰባት ተኩል
(በጩኸታ) እንግዲህ ታክሲውን ለሰባት ሰዓት ይዘዙልኝ!
አንድሬያስ	አደርጋለሁ

ውይይቱን ታደምጥ የነበረችው ኤክስ ሰውዬውን መስላ ለመናገር (ለማሾፍ) ትሞክራለች። ይህ ደግሞ አንድሬያስን ያስቆጣል።

| | |
|---|---|
| ኤክስ | እዚህ መዝፈን ይቻላል? |
| አንድሬያስ | የለም፣ አትችይም! |
| ኤክስ | እዚህ መረበሽ ይቻላል? |
| አንድሬያስ | ኤክስ፣ እለምንሻለሁ - እባክሽ ዝም በይ! |

በመሃሉ አንድ ባልና ሚስት ወደ እንግዳ መቀበያው መጥተዋል። እነርሱም በሚቀጥለው ቀን ማለዳ በሰባት ሰዓት መቀስቀስ ይፈልጋሉ።

| | |
|---|---|
| ሴትዮዋ | እንዴት አመሹ |
| አንድሬያስ | እንዴት አመሻችሁ |
| ሴትዮዋ | ነገ ማለዳ ሊቀሰቅሱን ይችላሉ? |
| አንድሬያስ | በደስታ፣ እና በስንት ሰዓት? |
| ሰውዬው | በሰባት ከሩብ |
| አንድሬያስ | አደርጋለሁ። በሰባት ከሩብ እቀሰቅስዎታለሁ |
| ሴትዮዋ | አመሰግናለሁ |
| አንድሬያስ | መልካም ሌሊት (ደህናደሩ) |

## Lektion 8

### አታድርጊ !

አንድሬያስ ከቤቱ ተቀምጦ ሙዚቃ እያደመጠ እራቱን በመብላት ላይ ነው። በዚሁ ጊዜም ስልክ ይደወላል። አንድሬያስ ኤክስ ስልኩን እንዳታነሳ ቢከለክልም ወደዚያው ትሄዳለች።

| | |
|---|---|
| ኤክስ | አንድሬያስ፣ ስልኩ እየተጣራ ነው |
| አንድሬያስ | (አፉ እንደሞላ) አዎን፣ እሰማለሁ! |
| | (ስልኩ መጣራቱን ይቀጥላል) |
| ኤክስ | ላንሳው እንዴ? |
| አንድሬያስ | የለም! አታድርጊ! እኔ ራሴ አነሳዋለሁ |
| ኤክስ | (ስልኩን ታነሳለች) ሄላው፣ እዚህ ሺፈር ቤት - |
| | አንድሬያስ? – አለ። ላምጣው? |
| አንድሬያስ | (ስልኩን ይነጥቅና) አንድሬያስ ሺፈር |

የደወለችው የአንድሬያስ እናት ናት። አንድሬያስን በሣምንቱ መጨረሻ ልትጎበኘው እንደፈለገች ትነግረዋለች።

| | |
|---|---|
| ወሮ/ሺፈር | እንዴት አመሸህ ልጄ |
| አንድሬያስ | ሄላው፣ እማዬ! እንደምነሽ? |
| ወሮ/ሺፈር | ንገረኝ እስቲ፣ ማን ነበር እሱ? |
| አንድሬያስ | ኦህ፣ አንዲት ጓደኛዬ |
| ወሮ/ሺፈር | እንዲህ ነው! ደህና፣ ይችን የግድ ከእኛ ማስተዋወቅ አለብህ |

አንድሬያስ ምን አባክሽ?
ወሮ/ሺፈር የለም፣ እንዲህ ማለቴ አይደለም! ስማ፣ ልንጎበኝህ እንፈልጋለን

አንድሬያስ በዚያ ቅጸሜ መስራት ቢኖርበትም ወላጆቹ በአንድ ሰዓት አኽን ይገባሉ። አንድሬያስም ስራውን የሚጨርሰው በዚያው ሰዓት ነው።

አንድሬያስ ግሩም! እና መቼ?
ወሮ/ሺፈር አሁን - በሣምንቱ መጨረሻ
አንድሬያስ ያሳዝናል! ቅጸሜ ዕለት መስራት አለብኝ
ወሮ/ሺፈር ለመሆኑ እስከ መቼ ነው የምትሰራው?
አንድሬያስ እስከ አንድ ሰዓት
ወሮ/ሺፈር ታዲያ ይቻላል! እንግዲህ ቅጸሜ እንመጣለን
በአንድ ሰዓት እዚያ ነን
አንድሬያስ ኦኬይ፣ እስከዚያው!

## Lektion 9
**ለእኔ ሙዝ!**

አንድሬያስ ምን መገበየት እንደሚኖርበት ለማጣራት ማቀዝቀዣው ውስጥ ይመለከታል። የሚያረጋግጠው ማቀዝቀዣው ባዶ መሆኑን ነው።

አንድሬያስ (በመራገም)ባዶ! ጨርሶ ባዶ!
ኤክስ አንድሬያስ፣ ምን ተፈጠረ? ተናደሃል እንዴ?
አንድሬያስ አዎን! የለም! ማቀዝቀዣው እንደገና ባዶ ሆኗል
ኤክስ እንግዲያማ መገበየት አለብህ!
አንድሬያስ እሱን ራሴ አውቀዋለሁ! አሁን ጸጥ በይ!

(አንድሬያስ ከራሱ እየተነጋገረ የሚያስፈልገውን ይጽፋል)

አንድሬያስ እንግዲህ ጸቦና ቅቤ ያስፈልገኛል
ኤክስ ጸቦና ቅቤ፣ አይብና የአሳማ ስጋ(ሶሲጅ)
አንድሬያስ አዎን፣ አይብና ሶሲጅ - እና ፍራፍሬ
ኤክስ ለእኔ ሙዝ! እባክህ!
አንድሬያስ አያለሁ። ግን አሁን ነይ! ገበያ እንሂድ

አንድሬያስ ወደ ገበያ አጸራሽ ሄዶ አንዲት ሻጭ ዘንድ አይብና የአሳማ ስጋ ይገዛል።

ሻጭ እንዴት አመሹ፣ ምን ይፈልጋሉ?
አንድሬያስ ጥቂት የአሳማ ስጋ(ሶሲጅ)
ሻጭ ታዲያ ምን ያህል?
አንድሬያስ 150 ግራም
ሻጭ ሌላስ ነገር?

| | |
|---|---|
| አንድሪያስ | አዎን፣ ቁራጭ አይብ |
| ሻጭ | እና የትኛውን አይብ ነው የሚፈልጉት? |
| አንድሪያስ | የተራራውን አይብ፣ እባክዎ |
| ሻጭ | ሌላ ተጨማሪ ነገር? |
| አንድሪያስ | አይ፣ በቃ ይሄው ነው |
| ኤክስ | (በመፈንደቅ) የወይራ ፍሬ! የወይራ ፍሬ አለ! አንድ ለመቅመስ እችላለሁ? |
| ሻጭ | ተጨማሪ የወይራ ፍሬ ይፈልጋሉ? |
| አንድሪያስ | አይ፣ በጣም አመሰግናለሁ |
| ሻጭ | (ለራሷ በቀስታ) እንግዳ ነገር፣ እንግዳ ነገር! |

## Lektion 10
### ሁሉን ማወቅ ትፈልጊያለሽ

የአንድሪያስ ወላጆች ልጃቸውን ከሆቴሉ ይቀበሉታል። በዚሁ አጋጣሚም ከሆቴሉ ሃላፊ ከወሮ/በርገር ይተዋወቃሉ።

| | |
|---|---|
| አንድሪያስ | ሄላው፣ መጥታችኋል ለካ! |
| ኤክስ | ማን? |
| አንድሪያስ | ወላጆቼ። እና አንቺ አሁን ዝም በይ! |
| ወሮ/ሺፈር | ጤናይስልኝ፣ ልጄ<br>(ይተቃቀፋሉ) |
| አቶ ሺፈር | ሰላም፣ አንድሪያስ |
| አንድሪያስ | ሰላም፣ አባባ። ጉዞው እንዴት ነበር? |
| ወሮ/ሺፈር | ጥሩ። አመሰግናለሁ። ምንም ችግር አልነበረም |
| አንድሪያስ | ግሩም! እኔ ጨርሻለሁ። እንሂድ? |

(ወሮ/በርገር ትመጣለች)

| | |
|---|---|
| ወሮ/በርገር | ጤናይስጥልኝ |
| አንድሪያስ | እነዚህ ወላጆቼ ናቸው። እና እሳቸው ደግሞ አለቃዬ ወሮ/በርገር ናቸው |
| ወሮ/ሺፈር | በጣም ደስ ይለኛል፣ ወሮ/በርገር። የእኔ አንድሪያስ እንደማያስቸግርዎት ተስፋ አደርጋለሁ |
| ወሮ/በርገር | ጨርሶም! ሁሉን ነገር ይችላል። እንግዳ ተቀባይ፣ ጋዜጠኛ፣ በሆድ ተናጋሪ ነው |
| ወሮ/ሺፈር | ምን? በሆድ ተናጋሪ ነህ? |
| አንድሪያስ | አንሄድም እንዴ? |

ወሮ/ሺፈር በሆቴሉ መግቢያ አጸራሽ አንድ የበርገር ቤተሰብ ፎቶ ተሰቅሎ ታያለች። ይህን መነሻ በማድረግም ከወሮ/በርገር ጋር ስለ ቤተሰቧ ታወራለች።

| | |
|---|---|
| ወሮ/ሺፈር | ሚስጥር እንዲባክን ለማድረግ አልፈልግም፣ ግን ያ ቤተሰብዎ እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ፣ አይደል? |
| ወሮ/በርገር | አዎን፣ ልክ ነው። እዚህ ፊት ያሉት እህቴና ወንድሜ ናቸው ይህች ደግሞ እኔ ነኝ |
| ወሮ/ሺፈር | ወዲያው ነው የሚለየው። እና እህትና ወንድምዎም አኽን ነው የሚኖሩት? |
| ወሮ/በርገር | የለም፣ እህቴ የምትኖረው ሚዩኒክ ነው። እዚያ ተጋብታ ነው ያለችው |
| ወሮ/ሺፈር | ወንድምዎስ? |
| ወሮ/በርገር | እሱ ፍራንክፈርት ነው ያለው |
| ወሮ/ሺፈር | እና ወላጆችዎስ? አኽን ውስጥ ናቸው? |
| ወሮ/በርገር | አይ፣ ሁለቱም ሞተዋል |
| ወሮ/ሺፈር | ኦህ፣ በጣም አዝናለሁ |
| አንድሬያስ | አንቺ እኮ ሁሉንም ነገር ለማወቅ ትፈልጊያለሽ! |
| ወሮ/በርገር | ምንም አይደል! |

## Lektion 11
### ምናልባት ቲያትርቤት?

አንድሬያስ ከወላጆቹ ጋር አኽን ውስጥ በምትገኝ አንዲት ትንሽ ቡና ቤት ተቀምጧል። ከቀትር በኋላ ምን እንደሚያደርጉ አብረው እያሰቡ ነው።

| | |
|---|---|
| አቶ ሺፈር | ታዲያ ዛሬ ምንድነው የምናደርገው? |
| ወሮ/ሺፈር | እኔ ዛሬ ከቀትር በኋላ የግድ ገበያ መሄድ እፈልጋለሁ |
| አንድሬያስ | ግብይት? |
| ወሮ/ሺፈር | አዎን፣ የማጣሪያ ሽያጭ ጊዜ ነው |
| አንድሬያስ | ልክ ነው! አንተስ፣ አባባ? |
| አቶ ሺፈር | እኔ ወደ ጋዜጣው መዘክር ብሄድ ደስ ይለኛል |
| ወሮ/ሺፈር | ወደ ካቴድራሉ ለመሄድም እንፈልጋለን |
| ኤክስ | እኔ ደግሞ ወደ ዳንስ ቤት (ዲስኮ) |
| አንድሬያስ | ኤክስ፣ ዝም በይ! |
| ወሮ/ሺፈር | አህ፣ ጊደኛህ ነበረች መሰለኝ! የት ናት ያለችው? |

አንድሬያስ በበኩሉ ሁሉም ማምሻውን በስድስት ሰዓት እንደገና ተገናኝተው ምግብ እንዲበሉና ከዚያም ምናልባት ቲያትርቤት እንዲሄዱ ሃሣብ ያቀርባል።

| | |
|---|---|
| አንድሬያስ | ደህና፣ ወደ ካቴድራሉ ነገም ልንሄድ እንችላለን። የጋዜጣው መዘክር ግን የሚከፈተው ቅዳሜ ቅዳሜ ብቻ ነው |
| ወሮ/ሺፈር | መደብሮቹም ዛሬ ብቻ ነው የሚከፈቱት |
| አቶ ሺፈር | እሱ ልክ ነው |

| | |
|---|---|
| አንድሬያስ | አንድ ሃሳብ አለኝ፡ እማዬ፣ አንቺ ገበያ ትሄጃለሽ- እኔ ከአባባ ጋር ወደ ጋዜጣው መዘክር እሄዳለሁ- እና በስድስት ሰዓት አብረን ለመመገብ እንሄዳለን |
| ወሮ/ሼፈር | ከዚያስ? ወዴት ነው የምንሄደው? |
| አንድሬያስ | ምናልባት ቲያትርቤት? |
| አቶ ሼፈር | አዎን! ሃሳቡ ጥሩ ነው |
| ወሮ/ሼፈር | ሌላስ ምን ነገር አለ? |
| አንድሬያስ | ጋዜጣ አለኝ እዚህ |

## Lektion 12
### ትምሕርቱ ደህና ነው?

ወሮ/ሼፈር ለመገብየት ትሄዳለች። አንድሬያስ አሁንም ከአባቱ ጋር ቡና ቤት እንዳለ ነው። ሁለቱ በዚሁ አጋጣሚ ጥቂት ይወያያሉ።

| | |
|---|---|
| ወሮ/ሼፈር | እንግዲህ፣ እስከ በኋላ |
| አንድሬያስ | ሰላም! (ቻዎ!) |
| አቶ ሼፈር | ቻዎ፣ እስከ ስድስት ድረስ! |
| | (ወደ አንድሬያስ ዞር በማለት) እሺ፣ አንተ እንዴት ነህ? |
| አንድሬያስ | አመሰግናለሁ፣ እኔ ደህና ነኝ። እናንተስ? |
| አቶ ሼፈር | እናትህ በጣም ደህና ናት |
| አንድሬያስ | አንተስ? |
| አቶ ሼፈር | እኔም ደህና ነኝ፣ ግን ችግር አለኝ |
| አንድሬያስ | ችግር? |
| አቶ ሼፈር | (ፈገግ እያለ) አዎን! ኮምፒዩተር አስቸግሮኛል |
| አንድሬያስ | ኮምፒዩተር አለህ? በሱስ እርግጥ ልረዳህ እችላለሁ! |
| አቶ ሼፈር | ይመስልሃል? |
| አንድሬያስ | በእርግጥ! |

በውይይቱ ሁለተኛ ክፍል አቶ ሼፈር አንድሬያስን ስለ ትምሕርቱና ስለ ስራው ይጠይቀዋል።

| | |
|---|---|
| አቶ ሼፈር | አንተስ፣ አንድሬያስ? ትምሕርቱ እንዴት ነው? |
| አንድሬያስ | ትምሕርቱ ደህና ነው |
| አቶ ሼፈር | አሁንስ ምን እያደረግህ ነው? |
| አንድሬያስ | በቅርቡ ስለ አኽን አንድ ዘገባ አዘጋጃለሁ |
| አቶ ሼፈር | አሀ፣ ግሩም ነው! ታዲያ ዘገባውን ትልክልናለህ? |
| አንድሬያስ | በእርግጥ! |
| አቶ ሼፈር | ስራውስ እንዴት ነው? |
| አንድሬያስ | መልካም! ስራውን እወደዋለሁ |

አቶ ሺፈር ከወሮ/በርገር ጋርስ?

አንድሬያስ በዕውነቱ በጣም ደግ ናት!

አቶ ሺፈር አዎን፤ እኔም ይመስለኛል

አንድሬያስ አሁን ወደ ጋዜጣው መዘክር እንሄድ?

አቶ ሺፈር አዎን፤ በደስታ

## Lektion 13

### በጥቁርም አለዎት?

ወሮ/ሺፈር አንድ መደብር ውስጥ ናት። የማጣሪያ ሽያጭ ወቅት በመሆኑ መደብሩ በጣም ሞልቷል። ብዙው የልብስ ዓይነት በርካሽ ዋጋ ነው የሚሸጠው።

ወሮ/ሺፈር ኡህ - እንዴት ሞልቷል!

(የድምጽ ማጉያ ማሳሰቢያ)

ውድ ደምበኞች! ምድር ቤት ውስጥ ያለ ልዩ አቅርቦታችን አያምልጣችሁ! የሴት ሸሚዝ -አራት ማርክ ብቻ!

(የገበያተኛው ኹከት)

ወንድ የት ነው መክፈል የሚቻለው?

1. ሴት ተመልከች፤ እንዴት ነው?

2. ሴት እስቲ አምጪ (አሳዪኝ)

(የድምጽ ማጉያ ማሳሰቢያ)

ውድ ደምበኞች! ምድር ቤት ውስጥ ያለ ልዩ አቅርቦታችንንም ተመልከቱ! ሹራብ - አስር ማርክ ባቻ!

ወንድ ሂሳብ መክፈያው እዚህ የት ነው?

ወሮ/ሺፈር የለም - ሲበዛ ይሞላብኛል

ወሮ/ሺፈር የሴቶች ዕቃ ወደሚሸጥበት ክፍል ትሄዳለች። እዚያ መደበኛ ሽያጭ የሚካሄድ በመሆኑ ቅናሽ አልተደረገም። ወሮ/ሺፈር አንድ ቀሚስ ነው የምትፈልገው። ግን ምን ዓይነት እንደምትፈልግ በውል አታውቅም።

ወሮ/ሺፈር ሊረዱኝ ይችላሉ? ቀሚስ ነው የምፈልገው

ሻጭ ሴት አዎን፤ በደስታ። ስንት ቁጥር?

ወሮ/ሺፈር 44

ሻጭ ሴት ቀለሙስ?

ወሮ/ሺፈር ምን ዓይነት ነው ያለዎት?

ሻጭ ሴት ይመልከቱ: እዚህ አንድ በቢጫ አለን
ይሄ አዲሱ የበልግ ቀለም ነው

ወሮ/ሺፈር አይ የለም - ቢጫ አልወድም! በጥቁርስ አለዎት?

ሻጭ ሴት አንድ ጊዜ! አገዛለሁ፤ ቁጥር 42 ብቻ ነው የቀረው

ወሮ/ሺፌር　እርሱ በእርግጥ ትንሽ ነው

ሻጭ ሴት　እስቲ ይሞክሩት! እዚያ ኋላ አንድ ልብስ መሞከሪያ ክፍል አለ

ወሮ/ሺፌር ቀሚሱን ትሞክራለች። በእርግጥም ያንሳታል።

ወሮ/ሺፌር　የለም፣ ሲበዛ ያንሰኛል

ሻጭ ሴት　አዝናለሁ!

ወሮ/ሺፌር　በጣም አመሰግናለሁ! ደህና ሁኑ

ሻጭ ሴት　ደህና ሁኑ

## Lektion 14

### የሚስብ ሳይሆን አይቀርም

እንድሬያስና ወላጆቹ በቦቶ ሽትራውስ የተደረሰው (ትልቅና ትንሽ) የተሰኘ ትርዒት ወደሚታይበት ቲያትርቤት ይሄዱ እንደሆነ ማውጣት ማውረድ ይዘዋል። የድርሰቱ ርዕስ ምን ትርጉም ሊኖረው እንደሚችልም ያስባሉ።

አንድሬያስ　ከተማ ቲያትርቤት ውስጥ የቦቶ ሽትራውስ ትርዒት አለ "ትልቅና ትንሽ"

አቶ ሺፌር　በጣም የሚስብ (የሚማርክ) ሳይሆን አይቀርም

ወሮ/ሺፌር　እና እሱ ምን ማለት ነው፣ ትልቅና ትንሽ"?

ኤክስ　ይህ ማለት: ሰዎች እንዴት ናቸው? ትልቅ ወይስ ... ትንሽ!

ወሮ/ሺፌር　(በመቆጣት) እንዴት ናቸው ሰዎች? ትልቅ ወይስ ትንሽ?!

አንድሬያስ　የለም! እንደሱ ማለት አይደለም!

ወሮ/ሺፌር　(አሁንም በቁጣ) አይ፣ በዕውነቱ፣ ስሜት አይሰጠኝም

አቶ ሺፌር　"ትልቅና ትንሽ" ሲባል እኮ እኛን ሰዎችን ነው የሚመለከተው

ኤክስ　ትልቅ ውይስ ትንሽ?

አቶ ሺፌር　ምን ያስባሉ?

ኤክስ　ብዙ ወይስ ትንሽ?

አቶ ሺፌር　እንዴት ነው አድራጎታቸው?

ኤክስ　ጥሩ ወይስ መጥፎ?

ወሮ/ሺፌር　እና ይህ ነው የሚስበው? እኔ በበኩሌ ይህችን ድምጽ ነው የምትስብ አድርጌ የምመለከተው!

ሶስቱም የቤርት ብሬሽትን "ሶስት ሣንቲም ኦፔራ" ለማየት ይስማማሉ።

አንድሬያስ　ምን ታስባላችሁ? ኦፔራው ቤት ውስጥ "የሶስት ሣንቲሙ ኦፔራ" አለ

ኤክስ　"የሶስት ሣንቲሙ ኦፔራ" ትርጉም ምንድነው?

አንድሬያስ　ሶስት ሣንቲም ማለት ርካሽ ማለት ነው

| | |
|---|---|
| ወሮ/ሺፈር | እስቲ ንገረኝ፡ ከማን ጋር ነው የምታወራው? |
| ኤክስ | ከእኔ ጋር! |
| አንድሬያስ | ኤክስ፣ ዝም በይ አባክሽ! |
| ወሮ/ሺፈር | ልረዳህ አልቻልኩም አንድሬያስ፣ ዕውነት በሆድ ተናጋሪ ነህ? |
| አንድሬያስ | አይ፣ እሱን በኋላ አስረዳሻለሁ። ይህና፣ ወደ "ሶስት ሣንቲሙ ኦፔራ" እንሂድ? |
| አቶ ሺፈር | አዎን፣ በደስታ |
| አንድሬያስ | የማኪ ሜሰርን ዜማ ታውቂ ይሆናል |
| ኤክስ | (ይህንኑ ዜማ ታዜማለች) |

## Lektion 15

### ማኪ ሜሰር የተሰኘ ሰው

አንድሬያስ ቲኬቶች ለማዘዝ ወደ ኦፔራ ቤቱ ስልክ ይደውላል።

| | |
|---|---|
| ሴት | እንዴት አመሹ |
| አንድሬያስ | እንዴት አመሹ፣ ሺፈር እባላለሁ። ለ"ሶስት ሣንቲሙ ኦፔራ" የቀረ ቲኬት አለ? |
| ሴት | ለመቼ? |
| አንድሬያስ | ለዛሬ ምሽት |
| ሴት | አዎን፣ ግን ሰላሣ ማርክ የሚያወጣ ብቻ |
| አንድሬያስ | ሶስት ቲኬቶች እወስዳለሁ |
| ኤክስ | አራት! |
| ሴት | ምን አሉ? ሶስት ነው ወይስ አራት የሚፈልጉት? |
| አንድሬያስ | የለም፣ ሶስት ብቻ ነው የምፈልገው |
| ሴት | ማን ነበር ስምዎ? |
| አንድሬያስ | ሺፈር |
| ሴት | ቲኬቶቹን እስከ ሰባት ተኩል መውሰድ ይኖርብዎታል |
| አንድሬያስ | አዎን፣ አደርጋለሁ። ይህና ሁኑ |
| ሴት | ይህና ሁኑ |

አንድሬያስ አሁን ስለ"ሶስት ሣንቲሙ ኦፔራ" ያስረዳል።

| | |
|---|---|
| አንድሬያስ | እንግዲህ፡ የሶስት ሣንቲሙ ኦፔራ ታሪክ የሚፈጸመው ለንደን ውስጥ ነው። ዘራፊዎችንና ለማኞችን ነው የሚመለከተው። አለቃቸው አንድ ማኪ ሜሰር የተሰኘ ሰው ነው። ማኪ ሜሰር ጩቤ እንዳለው ከስሙ መረዳት ይቻላል። |
| ኤክስ | ግልጽ ነው! |
| አንድሬያስ | የመጀመሪያው ዜማ ስለ ማኪ ሜሰር ድርጊቶች ያወሳል። |

አንድ ሰው ሞተ። ሰውዬው ገንዘብ ነበረው። ግን ገንዘቡ ጠፋ። እና አሁን ገንዘቡ ሜኪ ሜሰር ዕጅ ነው።

ኤክስ ዘረፈው

## Lektion 16

### የሆነ ሰው ሰምቷል

አንድሬያስ ኤክስን እንዴት እንደተዋወቃት ለወላጆቹ ያወራል።

አንድሬያስ ይሄን ታሪክ መቼም አታምኑኝም! ይህና፣ እንዲህ ነበር ፤ ከቤት ሆኜ አንድ መጽሐፍ እያነበብኩ ነበር -ኮሎኝ አጠገብ ይኖሩ ስለነበሩት "ሃይንሰልሜንሽን"! እነዚህ በጎ መናፍስት ሁሌ ሌት ወደ ከተማ እየመጡ የሰዉን ስራ ያከናውኑ ነበር ይባላል። ታዲያ ታሪኩን አንብቤ አለምኩ... እና"እኔም ይህን መሰሉን ዕርዳታ እፈልጋለሁ! "ስል በመጮህ ተናገርኩ። ከዚያ በኋላም " ግን ይህን መሰሉ ነገር በዚህም በዚያም አይገኝም"! አልኩ

ወሮ/ሼፈር እና ከዚያስ?

አቶ ሼፈር ኡስ! ዝም!

አንድሬያስ የሆነ ሰው ሰምቶ ነበር

ወሮ/ሼፈር ማን?

አንድሬያስ ኤክስ! እና እንዲህ አለች

ኤክስ ሄላው፣ እዚህ ነኝ!

የአንድሬያስ ወላጆች ነገሩን በተለያየ መልክ ነው የተቀበሉት። ወሮ/ሼፈር ጥቂት ግራ ሳትጋባ አልቀረችም። አቶ ሼፈር በበኩሉ ኤክስ አንድሬያስን ትረዳው እንደሆን -- ለማወቅ ይፈልጋል።

ኤክስ ሄላው፣ እዚህ ነኝ!

ወሮ/ሼፈር የት? የት ናት? አላያትም!

ኤክስ የምታይ ነገር አይደለሁም

ወሮ/ሼፈር እና ይሄን ሁሉ ልናምን ነው?

ኤክስ በዚህም በዚያም

አቶ ሼፈር መልካም፣ አንድሬያስ፣ ለመሆኑ ታግዝሃለች?

አንድሬያስ (አንድሬያስ እያፈረ ጉሮሮውን ያጠራል)

ኤክስ አዎን፣ በጣም!

## Lektion 17

### የአኸን መጠሪያ ከየት ነው የመነጨው?

አንድሪያስ ይቅርታ ያድርጉልኝ፣ አንድ ነገር ልጠይቅዎት እፈልጋለሁ

1. ተላላፊ አዝናለሁ፣ እኔ እዚህ ባዕድ ነኝ

አንድሪያስ ይቅርታ ያድርጉልኝ፣ አንድ ነገር ልጠይቅዎት እፈልጋለሁ

2. ተላላፊ እሺ፣ ምን?

አንድሪያስ የአኸን ስያሜ ምን ትርጉም ያለው ይመስልዎታል?

2. ተላላፊ አኸን? እንዴት ማለትዎ ነው?

አንድሪያስ አዎ፣ የአኸን መጠሪያ ከየት ነው የመነጨው?

2. ተላላፊ አይ፣ አላውቀውም። እርስዎ ያውቁታል?

አንድሪያስ ቀጥሎም አንዲት ወጣት ተላላፊን ይጠይቃል።

አንድሪያስ ጤናይስጥልኝ፣ አንድ ጥያቄ አለኝ

1. ተላላፊዋ እሺ፣ ምን?

አንድሪያስ የአኸን መጠሪያ ትርጉም ምንድነው?

1. ተላላፊዋ አላውቅም፣ የማወቅ ፍላጎትም የለኝ

አንድ አንጋፋ ባልና ሚስት መልሱን ያገኛሉ።

አንድሪያስ የአኸን መጠሪያ ትርጉም ምን እንደሆነ ልጠይቅዎት እችላለሁ

3. ተላላፊ አኸን? አኸን?

አንድሪያስ አዎን፣ የአኸን መጠሪያ ከየት የመነጨ ነው?

3. ተላላፊ ይህና ጥንት ሮማውያን እዚህ ነበሩ

አንድሪያስ ትክክል

2. ተላላፊዋ እና አኸን ውስጥ ጥንትም ምንጮቹ ነበሩ

3. ተላላፊ ልክ ነው! እና ውሃ የሚጠራው "አኩዋ" እየተባለ ነበር

2. ተላላፊዋ ስለዚህ የአኸን ስም ከ"አኩዋ" የመነጨ ሲሆን ትርጉሙም
ውሃ ማለት ነው

አንድሪያስ አዎን፣ የአኸን የመጀመሪያ መጠሪያ "አኩዋ" ነበር

3. ተላላፊ ይቆዩ - እና በኋላም ጌርማኖች እዚህ ነበሩ

አንድሪያስ እነርሱ ናቸው ለአኸን "አሃ" የሚል ስያሜ የሰጡት

2. ተላላፊዋ "አሃ"ም ውሃ ማለት ነው

አንድሪያስ አዎን!

## Lektion 18

### ከርሱ ነው የማውቀው

አንድሪያስ ከወላጆቹ ጋር አኸንን እየተዘዋወረ ይጎበኛል። እዚያ ብዙ ምንጮች ይገኛሉ። ለምሳሌ ውሃው የሚጠጣው ኤሊዘን ምንጭ!

| | |
|---|---|
| አቶ ሺፈር | አንድሬያስ፣ ከተማይቱን ታሳየናለህ? |
| ኤክስ | ኦህ አዎን! |
| አንድሬያስ | (እንጸስጎብኚ) ታውቃላችሁ፡ አኽን የውሃ ከተማ እንደሆነች |
| ኤክስ | በዚህም በዚያም! አኽን ማለት ውሃ ማለት ነው |
| ወሮ/ሺፈር | ይሄን ደግሞ እሷ ከየት ነው የምታውቀው? |
| ኤክስ | ከርሱ ነው የማውቀው፣ ከአንድሬያስ |
| ወሮ/ሺፈር | ግን እኮ አኽን ባሕር ላይ አይደለም የምትገኘው |
| አንድሬያስ | ልክ ነው! ግን አኽን ብዙ ምንጮች አሏት |
| ወሮ/ሺፈር | ውሃውን መጠጣት ይቻላል? |
| አንድሬያስ | በመሠረቱ አይቻልም። ይህ ከ 1827 ዓም ወዲህ የሚታወቀው ኤሊዘን ምንጭ ነው። ውሃውን መጠጣትም ይቻላል |
| ወሮ/ሺፈር | ለመቅመስ እፈልጋለሁ! |
| ኤክስ | ግን ጣዕሙ አስከፊ ነው! |
| ወሮ/ሺፈር | ይሄን ደግሞ ከየት ነው የምታውቀው? |
| አንድሬያስ | እኔ ነኝ የነገርኳት |
| ወሮ/ሺፈር | (ውሃውን ትቀምሳለች)ሥ - ጣዕሙ በዕውነትም አስከፊ ነው! |
| አንድሬያስ | ግን በጣም ጤናማ ነው! |

ሶስቱም ዙረታቸውን ይቀጥሉና አንድሬያስ ዝነኛውን የአኽን ዶም(ካቴድራል)ያሳያቸዋል። ጥንት የንጉሠ-ነገሥት ካርል ታላቁ መቀመጫ የሚገኘው በዚህ ስፍራ ነበር።

| | |
|---|---|
| አንድሬያስ | ይሄ ነው ካቴድራሉ! |
| አቶ ሺፈር | እዚህ ነበር ጥንት የካርል ታላቁ መቀመጫ፣ አይደል? |
| አንድሬያስ | ልክ ነው! የካርል ታላቁ መቀመጫ እዚህ ነበር |
| ኤክስ | ካርል ታላቁ? |
| አንድሬያስ | አንድ ንጉሠ-ነገሥት ነበር |
| ኤክስ | እና ለምንድነው አኽን ውስጥ የነበረው? |
| አንድሬያስ | አኽን ብዙ ሞቃት ምንጮች አሏት። እና ይሄ ጥንትም በጣም አስደሳች ነበር |
| ኤክስ | ታዲያ ምንጮቹን ታሳየኛለህ? |
| አንድሬያስ | ኦኬይ፣ ኤክስ፣ ቃል እገባልሻለሁ! |
| ወሮ/ሺፈር | እኔ ደግሞ አሁን ካቴድራሉ ውስጥ መግባት እፈልጋለሁ |
| አቶ ሺፈር | መልካም - አሁን እንገባለን |

## Lektion 19

### እንዴት ነው ሰው ከንጉሠ-ነገሥት የሚያወራው?

አንድሬያስ ሮማ ውስጥ በ 800 ዓም ንጉሠ-ነገሥት ሆኖ ዘውድ ከጫነው ከካርል ታላቁ ጋር አንድ ልብ-ወለድ ቃለ-ምልልስ ያካሂዳል።

| | |
|---|---|
| ኤክስ | ከአንድ ንጉሠ-ነገሥት ጋር ቃለ-ምልልስ ታደርጋለህ? |
| አንድሬያስ | አዎን፣ ግን አባክሽ ዝም በይ! |
| ኤክስ | ተደናግጠሃል እንዴ? |
| አንድሬያስ | እርግጥ! እንዴት ነው ሰው ከንጉሠ-ነገሥት የሚያወራው? |
| ድምጽ | ማሳሰቢያ! ስርጭቱ ይጀምራል |
| አንድሬያስ | ጤናይስጥልኝ አድማጮች! ዛሬ በስቱዲዮአችን አንድ እንግዳ<br>አሉን። ካርክ ታላቁ እዚህ ናቸው! እንኳን ደህና መጡ! |
| ካርል ታላቁ | ጤናይስጥልኝ፣ ወጣት ሰው |
| አንድሬያስ | ከአንድ ጉዞ በቀጥታ መመለስዎ ነው? |
| ካርል ታላቁ | አዎን፣ ሮማ ነበርሁ |
| አንድሬያስ | አሁን ንጉሠ-ነገሥት … ነዎት |
| ካርል ታላቁ | ታላቅ ክብር ይሰማኛል |
| አንድሬያስ | ጀርመናውያን "ካርል ታላቁ" ብለው ነው የሚጠሩዎት |
| ካርል ታላቁ | ዕውነት? ይህ ታዲያ የካርሎስ ማግኑስ ትርጉም መሆኑ ነው? |
| አንድሬያስ | ልክ ነው! ፈረንሳዮች ደግሞ "ቻርለማኝ" እያሉ ይጠሩዎታል |
| ኤክስ | ጣሊያኖች ደግሞ "ካርሎ ማግኖ" |
| ካርል ታላቁ | እንዴት? |

አንድሬያስ ካርል ታላቁ አኸን ውስጥ በዛሬው ጊዜም እጅግ ዝነኛ እንደሆነ ይነግረዋል። በካርል ስም የሚጠሩ አንድ ምንጭና አንድ ሽልማት አሉ። Karls ምንጭ እና Karls ሽልማት!

| | |
|---|---|
| አንድሬያስ | አኸን እንዴት ናት? |
| ካርል ታላቁ | አኸንን እወዳታለሁ - በተለይ ምንጮቿን! ሙቀቱ ይስማማኛል<br>እርስዎስ -አኸን ውስጥ ስንት ጊዜዎ ነው? |
| አንድሬያስ | ከአንድ ዓመት ወዲህ |
| ካርል ታላቁ | እና አኸን ዛሬ እንዴት ናት? |
| አንድሬያስ | እርስዎ በጣም ዝነኛ ነዎት -ዛሬም |
| ካርል ታላቁ | ዕውነት? |
| አንድሬያስ | አኸን ውስጥ ካርልስ ምንጭ አለ … |
| ካርል ታላቁ | ይህ ለእኔ ክብር ነው |
| አንድሬያስ | ካርልስ ሽልማት አለ … |
| ካርል ታላቁ | ካርልስ ሽልማት? |
| አንድሬያስ | አዎን፣ ለአውሮፓ አንድነት |
| ካርል ታላቁ | አህ አውሮፓ! በመላው ዓለም ጥሩ ግንኙነት ነበረኝ<br>ኮንስታንቲኖፕል … |

## Lektion 20

### ክፍል እንዲያዝልኝ አደርጌያለሁ

ወሮ/በርገር አንድሬያስ ከወላጆቹ ጋር የሣምንቱን መጨረሻ እንዴት እንዳሳለፈ ትጠይቀዋለች። አንድሬያስም የሶስት ሣንቲሙን ኦፔራ እንደተመለከቱ ይነግራታል።

| | |
|---|---|
| አንድሬያስ | ጤናይስጥልኝ፣ ወሮ/በርገር |
| ወሮ/በርገር | ጤናይስጥልኝ፣ አቶ ሼፈር። እንዴት ነው፣ ከወላጆዎችዎ ጋር ጥሩ ነበር? |
| አንድሬያስ | አዎን፣ አመሰግናለሁ! በጣም ጥሩ ነበር |
| ወሮ/በርገር | ምን አደረጉ? |
| አንድሬያስ | አኸንን ለወላጆቼ አሳየሁ |
| ወሮ/በርገር | እና? ወደዱት? |
| አንድሬያስ | አስባለሁ። ቲያትርቤትም ነበርን። የሶስት ሣንቲሙን ኦፔራ አየን |
| ኤክስ | እኔ አላየሁም! |
| ወሮ/በርገር | አሀ፣ መጣች እንደገና፣ ሁለተኛ ድምጽዎ! አብራ አልነበረችም? |
| ኤክስ | የለም፣ ያሳዝናል የለም! |

አንድ እንግዳ ክፍል እንዲያዝለት አዟል። ሆኖም ቀኑን አሳስቷል። እና ክፍሉን ያስያዘው ካሰበው አንድ ቀን አዘግይቶ ነው።

| | |
|---|---|
| አንድሬያስ | ጤናይስጥልኝ |
| አቶ ሙለር | ጤናይስጥልኝ፣ ክፍል አስይዤ ነበር |
| አንድሬያስ | ስምዎን ማን ልበል? |
| አቶ ሙለር | ሙለር፣ ዶር/ማርቲን ሙለር |
| አንድሬያስ | አሃ አዎን፣ ከጸሐፊዎ ጋር በስልክ ተነጋግሬ ነበር አንዴ ይጠብቁ! (አንድሬያስ የምዝገባ ደብተሩን ያገላብጣል) ይሄው - ክፍል 20 ግን - ክፍሉን ያስያዙት ለነገ ነው። ዛሬ ደግሞ ሆቴሉ ሞልቷል |
| አቶ ሙለር | ምን አሉ? የማይሆን ነው! ስህተት መሆን አለበት |
| አንድሬያስ | በጣም አዝናለሁ፣ ዶር ሙለር። ትዕዛዝዎን የመዘገብኩት ለ 14 ነው |
| አቶ ሙለር | ለአስራ አራት? |
| አንድሬያስ | አዎን! ዛሬ ደግሞ ገና አስራ ሶስት ነው |
| አቶ ሙለር | ግልጽ ነው፣ እኔም አውቃለሁ። (ጠለቅ አድርጎ በመተንፈስ) አስራ ሶስት፣ ገደ ቢስ ቀን! እና አሁን ምን ላድርግ? |

አንድሬያስ አንድ ጊዜ ይጠብቁ! አለቃዬን አነጋግራታለሁ

አቶ ሙለር አመሰግናለሁ!(ለራሱ)እንዲህ ዓይነት ክንቱ ነገር!

## Lektion 21

### ፖስታ ቤት እንዴት መድረስ እችላለሁ?

*አቶ ሙለር ወደ አኸኑ የጉባዔ ማዕከል ወደ "ኤውሮግሬስ" ለመሄድ ይፈልጋል። ሆኖም ይህን በማያሻማ ሁኔታ አይገልጽም።*

አንድሬያስ እንዴት አደሩ፣ ዶር/ሙለር

አቶ ሙለር እንዴት አደሩ

አንድሬያስ ጥሩ ተኙ?

አቶ ሙለር አዎን፣ አመሰግናለሁ! በጣም ጥሩ። እስቲ ይንገሩኝ፡ እንዴት ነው ወደ ማዕከል መድረስ የምችለው?

አንድሬያስ መዘጋጃ ቤቱንና ካቴድራሉን ነው ለማየት የሚፈልጉት?

አቶ ሙለር የለም -ይቅርታ ያድርጉልኝ፣ ወደ ጉባዔው ማዕከል መሄድ አለብኝ

አንድሬያስ አሃ፣ ኤውሮግሬስን ማለትዎ ነው?

አቶ ሙለር አዎን፣ ትክክል! ወደ ኤውሮግሬስ መሄድ አለብኝ

አንድሬያስ ሩቅ አይደለም። በአውቶቡስ መጓዝ ይችላሉ

አቶ ሙለር አይ የለም - ታክሲ ይዘዙልኝ አባክዎ!

አንድሬያስ እሺ፣ በደስታ

*አንዲት ሴት ወደ ቲያትር አደባባይ እንዴት እንደምትሄድ አንድሬያስን ትጠይቃለች።*

ሴትዮዋ ይቅርታ፣ ወደ ቲያትር አደባባይ መሄድ እፈልጋለሁ። እንዴት ነው ከዚያ የምደርሰው?

አንድሬያስ ሩቅ አይደለም። በእግር ለመሄድ ይችላሉ

ሴትዮዋ ግሩም ነው!

አንድሬያስ በመጀመሪያ ወደ ቀኝ፣ ከዚያም እንደገና ወደ ቀኝ፣ ከዚያም ያለማቋረጥ ቀጥታ ሲሄዱ ቲያትር አደባባይ ይደርሳሉ

ሴትዮዋ በጣም አመሰግናለሁ

*አንድ ወጣት ሰው ፖስታ ቤት ይፈልጋል።*

ሰውዬው ለመሆኑ ፖስታ ቤት የምደርሰው እንዴት ነው?
እዚህ በቅርቡ አንድ አለ?

አንድሬያስ አዎን፣ ወደ ባቡር ጣቢያ የሚወስደውን መንገድ ያውቃሉ?

ሰውዬው አዎን

አንድሬያስ እንግዲያው ገዛም ብለው ባቡር ጣቢያ ይሂዱ። እዚያ ፖስታ ቤትም አለ

ሰውዬው በጣም አመሰግናለሁ

*የማትታየዋ ኤክስም የማይታይ ጸጉሯን ጸጉር ሰሪ ዘንድ ሄዳ ለማሰራት ትፈልጋለች።*

| | |
|---|---|
| ኤክስ | እዚህ ቅርብ ጸጉር ሰሪ አለ? |
| አንድሬያስ | ወዴት መሄድ ነው የምትፈልጊው? |
| ኤክስ | ጸጉር ሰሪጋ ! |
| አንድሬያስ | ( ይተነፋፍሳል ) |

## Lektion 22

**ረቡዕ ዕለት፣ ማለጻ በሰባት**

አንጺት ሴት ክፍሏ ውስጥ የሚገኘው ሰውነት መታጠቢያ (ሻወር) መበላሸቱን ለአንድሬያስ በማስታወቅ አቤቱታ ታሰማለች።

| | |
|---|---|
| ሴትዮዋ | እንዴት አደሩ። አለቃውን ለማነጋገር እፈልጋለሁ |
| አንድሬያስ | እንዴት አደሩ። አንድ ጊዜ ይጠብቁ |

(አንድሬያስ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ይወጣና ይጣራል)

| | |
|---|---|
| | ወሮ/በርገር? ሃና፣ ወሮ/በርገር አንቺ ዘንድ አሉ? |
| ሃና | የሉም። ጥርሳቸውን አሟቸው ነበር። ጥርስ ሃኪምጋ ናቸው |
| አንድሬያስ | (ወደ እንግዳ መቀበያው ይመለስና) |
| | አዝናለሁ። አለቃዋ የሉም። ምናልባት እኔ ልረዳዎት |
| | እችላለሁ? |
| ሴትዮዋ | ተስፋ አደርጋለሁ። ክፍሌ ውስጥ ያለው ሻወር ተበላሽቷል |
| አንድሬያስ | ይቅርታ፣ ይህን አላወቅንም |
| ሴትዮዋ | ሌሊቱን ሙሉ ሲያንጠባጥብ ነው ያደረው። ጧት ደግሞ |
| | ሁሉም ነገር ረጥቧል |
| አንድሬያስ | ለአለቃዬ አስታውቃለሁ። በእርግጥ ሁሉንም ነገር እናስተካክላለን |
| ሴትዮዋ | ተስፋ አደርጋለሁ። ደህና ሁኑ |
| አንድሬያስ | ደህና ሁኑ |

ወሮ/በርገር ተመልሳ ከመጣች በኋላ የጥገና ቀጠሮ ለመውሰድ ወደ አንድ ኩባንያ ትደውላለች።

| | |
|---|---|
| ሰውዬው | ሞል ኩባንያ፣ ጤናይስጥልኝ |
| ወሮ/በርገር | ጤናይስጥልኝ፣ በርገር፣ ሆቴል አውሮፓ! አንድ ሻወር ተሰብሮብናል፣ |
| | ሠራተኛ መቼ ልትልኩልን ትችላላችሁ? |
| ሰውዬው | እስቲ ይጠብቁ፡ ዛሬ ሰኞ ነው፣ እንበል አርብ በዘጠኝ ሰዓት |
| ወሮ/በርገር | የለም! በጣም ይዘገያል። ቀደም ብሎ ሊሆን አይችልም? |
| | እጅግ አስቸኳይ ነው |
| ሰውዬው | ረቡዕ ዕለት፣ ማለዳ በዘጠኝ |
| ወሮ/በርገር | ዛሬ ወይም ነገ አይሆንም? |
| ሰውዬው | ደህና፣ እንበል ነገ፣ ግን ከምሽት በፊት አይሆንም |
| ወሮ/በርገር | ለደግነትዎ አመሰግናለሁ! እንግዲያው እስከ ነገ |

## Lektion 23

### ምን ተፈጠረ?

አንድሬያስ ከረጅም ጊዜ በፊት ወደ በርሊን ጋብዞት ለነበረው ለ ዶር/ትሁርማን ይደውላል። አንድሬያስ በዚህ አጋጣሚ የሚረዳው ዶር/ትሁርማን ራሱ ወደ አኼን እንደሚመጣ ነው።

| | |
|---|---|
| ዶር/ትሁርማን | ትሁርማን |
| አንድሬያስ | እንዴት አመሹ፣ ዶር/ትሁርማን። አንድሬያስ ሺፈር ነኝ፣ ከሆቴል አውሮፓ |
| ዶር/ትሁርማን | ኦህ አዎ! እንዴት አመሹ፣ አቶ ሺፈር |
| አንድሬያስ | ለረጅም ጊዜ አልደወልኩልዎትም። ይቅርታ ያድርጉልኝ |
| ዶር/ትሁርማን | ደህና! ምንም አይደል! |
| አንድሬያስ | ወደ በርሊን ጋብዘውኝ ነበር |
| ዶር/ትሁርማን | አዎን፣ ልክ ነው! ጋብዤዎት ነበር። ግን አሁን እኔ ወደ አኼን እመጣለሁ |
| አንድሬያስ | ግሩም ነው! ሆቴል አውሮፓ ውስጥ ለርስዎ ምንጊዜም ነጻ ክፍል አለ |
| ዶር/ትሁርማን | አውቃለሁ! ግን ክሊኒክ መግባት አለብኝ |
| አንድሬያስ | ኦህ - በጣም አዝናለሁ |

ዶር/ትሁርማን በመኪና አደጋ አጋጥሞት እንደነበር ያወሳል። ሆኖም ያን ያህል የከፋ ጉዳት አልደረሰበትም።

| | |
|---|---|
| ዶር/ትሁርማን | አደጋ አጋጥሞኝ ነበር |
| አንድሬያስ | በመኪና? |
| ዶር/ትሁርማን | አዎን |
| አንድሬያስ | እርስዎ ጉዳት ደረሰብዎት? |
| ዶር/ትሁርማን | የለም፣ ያን ያህል የከፋ አልነበረም |
| ኤክስ | ምን ተፈጠረ (ደረሰ)? |
| ዶር/ትሁርማን | ምን? የርስዎ ድምጽ ነበር? |
| አንድሬያስ | የለም - ምን ተፈጠረ? |
| ዶር/ትሁርማን | ከአንድ ጓደኛጋ መጣሁ። ከዚያም ወደ ቤቴ ተጓዝኩ - እና ከዚያም... አሀ፣ አኼን ውስጥ ላወራልዎት እችላለሁ |
| አንድሬያስ | በደስታ! |
| ዶር/ትሁርማን | ይምጡና ይጠይቁኝ! ማገገሚያው ክሊኒክ ውስጥ ነው የምቆየው |
| አንድሬያስ | ያለጥርጥር እጠይቅዎታለሁ |
| ኤክስ | እኔም! |
| አንድሬያስ | ደህና ሁኑ |
| ዶር/ትሁርማን | እስከ ቅርቡ - አኼን ውስጥ እስክንገናኝ |

## Lektion 24

### ረስቼው ነው

አንድሬያስ አኸን ውስጥ በሚገኝ አንድ ክሊኒክ ዶር/ትሁርማንን ይጎበኛል። ዶር/ትሁርማንም ደርሶበት ስለነበረው አደጋ ያጫውተዋል።

ዶር/ትሁርማን  አቤት፣ ይግቡ!

አንድሬያስ  ጤናይስጥልኝ፣ ዶር/ትሁርማን

ዶር/ትሁርማን  ጤናይስጥልኝ፣ አቶ ሼፈር

አንድሬያስ  እንዴነዎት?

ዶር/ትሁርማን  ደህና! በጣም ደህና! ግን እዚህ ጥቂት ይሰለቻል

አንድሬያስ  ያጋጠመዎት አደጋ እንዴት ነው የደረሰው?

ዶር/ትሁርማን  አላወራሁልዎትም?

አንድሬያስ  እርግጥ! ከአንድ ጓደኛጋ መጡ እና ወደ ቤት ተጓዙ፣
ግን ምንድነው የተፈጠረው?

ዶር/ትሁርማን  አዎን - አንድ የትራፊክ መብራት ፊት አቆምኩ - በእርግጥ ቀይ ነበር!

አንድሬያስ  ከዚያስ?

ዶር/ትሁርማን  ከኋላዬ ያለው መኪና ፈጥኖ ስለነበር ሾፌሩ በጊዜው ፍሬን
ሊይዝ አልቻለም - እና ግጭት ይደርሳል!

አንድሬያስ  እና እርስዎስ? ምን ደረሰብዎት?

ዶር/ትሁርማን  ብዙ አልነበረም። ግን አሁን አዘውትሮ ራስ ምታት አለብኝ
(ጥቂት እረፍት) አዎን፣ ታሪኬ ይሄ ነበር

አንድሬያስ ክሊኒኩ ውስጥ ስለሚሰጠው እንክብካቤ ዶር/ትሁርማንን ይጠይቃል።

ዶር/ትሁርማን  እርስዎስ! እንዴት ነዎት?

አንድሬያስ  ደህና፣ አመሰግናለሁ! ግን በቂ ጊዜ አልነበረኝም: ስራው፣
ትምሕርቱ፣ ከዚያም ወላጆቼ ጎበኙኝ እና ...

ዶር/ትሁርማን  እና ስለዚህ ነው ያልደወሉልኝ?

አንድሬያስ  ህም - አይደለም። ረስቼው ነው። በጣም አዝናለሁ

ዶር/ትሁርማን  ያውቃሉ፣ ጥቂት አሳዝነውኛል። ቢሆንም ያን ያህል ከፉ
ነገር አይደለም

አንድሬያስ  ለራስ ምታትዎ ምን ዓይነት ህክምና እየተደረገልዎት ነው?

ዶር/ትሁርማን  በእርግጥ ብዙ እታሻለሁ - ከዚያም ምንጮቹ! መቀቱ ይረዳኛል

ኤክስ  ይህን ካርል ታላቁም ተናግሮ ነበር!

ዶር/ትሁርማን  ካርል ታላቁ? በደምብ አልሰማም፣ ግን የርስዎ ድምጽ
አልነበረም፣ አቶ ሼፈር?

አንድሬያስ  የለም፣ የእኔ ድምጽ አልነበረም

ኤክስ  እኔ ነበርኩ!

ዶር/ትሁርማን  እንደማስበው፣ እርስዎም የሚነግሩኝ ታሪክ ያለ ይመስለኛል

## Lektion 25

### ፎጣዎችም ሊሰጡኝ ይችላሉ?

አንዲት ሴት አንድሬያስ ታክሲ እንዲያገዘላት ትጠይቃለች።

| | |
|---|---|
| ሴትዮዋ | ታክሲ ሊያዙልኝ ይችላሉ? |
| አንድሬያስ | አዎን በደስታ! እና ለመቼ? |
| ሴትዮዋ | እባክዎ አሁኑኑ |
| አንድሬያስ | አደርጋለሁ! አሁኑኑ አገዝልዎታለሁ |

በአንድ ክፍል ውስጥ ፎጣዎችም ይጎላሉ። እንግዳው ወሮ/በርገር እነዚሁኑ ታስመጣለት ዘንድ ይጠይቃል።

| | |
|---|---|
| ሰውዬው | ይቅርታ! ፎጣዎችም ሊሰጡኝ ይችላሉ?<br>መታጠቢያ ቤቱ ውስጥ አንድም የለ |
| ወሮ/በርገር | ይቅርታ፣ ዛሬ ስራ በዝቷል። ክፍል አጽጂዋ ፎጣዎቹን<br>አሁኑኑ ታመጣልዎታለች። ሃና! ሃና! |
| ሃና | አቤት? |
| ወሮ/በርገር | ለአቶ ብራውን ፎጣዎችም ታመጪላቸዋለሽ? |
| ሃና | ኡህ፣ ረስቼው ነው። አሁኑኑ አመጣላቸዋለሁ |

አሁን አንድሬያስና ወሮ/በርገር ስለ ዶር/ትሁርማን ለመነጋገር ጊዜ ያገኛሉ።

| | |
|---|---|
| ወሮ/በርገር | በነገራችን ላይ፣ ለዶር/ትሁርማን ደውዬ ነበር |
| አንድሬያስ | ዕውነት? የክሊኒኩ ቆይታ አሰልቺ ሆኖባቸዋል |
| ወሮ/በርገር | አዎን፣ ለእኔም ነግረውኛል። ስለዚህም ለዕሑድ<br>ጋብዣቸዋለሁ |
| አንድሬያስ | ዕውነት? |
| ወሮ/በርገር | አብረን የመርከብ ጉዞ እናደርጋለን። አብረውን<br>ለመሄድ አይፈልጉም? |
| ኤክስ | የመርከብ ጉዞ? |
| ወሮ/በርገር | ትክክል! ሁለተኛ ድምጽዎም አብራ ልትሄድ ትችላለች |
| ኤክስ | በዚህም በዚያም! አንድሬያስ፣ እባክህ! |

## Lektion 26

### ወደ ሎረላይ የሚደረግ ጉዞ ውብ ነው

አንድሬያስ፣ ወሮ/በርገር፣ ዶር/ትሁርማንና ኤክስ ራይን ወንዝ ላይ በሚገኝ አንድ የመርከብ ማረፊያ ተገናኝተዋል። አብረው የመርከብ ጉዞ ለማድረግ ይፈልጋሉ። ኮሎኝ ከተማንም የሚያቋርጠው ራይን እጅግ ታላቅ ወንዝ ነው።

| | |
|---|---|
| አንድሬያስ | እዚያ ብዙ ሰው ነው የተሰለፈው |

ዶር/ትሁርማን አያስደንቅም፣ በዚህ አየር!

አንድሬያስ ቲኬት እንደምናገኝ ተስፋ አደርጋለሁ

ወሮ/በርገር በእርግጥ።(በመተንፈስ)ኦህ - ወደ ሎረላይ የሚደረግ ጉዞ ውብ ነው

ኤክስ ሎረላይ?? አውቃታለሁ።(እንደማለም እያላት)እጅግ ውብ ነበረች

ዶር/ትሁርማን (ለራሱ)እንደገና ይህች ድምጽ መጣች...
(ለአንድሬያስ)የርስዎ ድምጽ አልነበረችም፣ አቶ ሼፈር?

ወሮ/በርገር የለም! ሁለተኛ ድምጹ ነበረች

ዶር/ትሁርማን ይህች ድምጽ ከየት ነው የምትመጣው?

ወሮ/በርገር (በውስጠ ፈገግ)አዎን፣ ይህ የአቶ ሼፈር ምስጢር ነው
(ወደ ኤክስ ዞር እንዳለች በማስመሰል)እሺ አንቺ ምስጢር -
ለመሆኑ የሎረላይን ዜማስ ታውቂያለሽ?

ኤክስ አይ

ወሮ/በርገር እንግዲያው በደምብ አድምጪ!
(የሎረላይን ዜማ ታዜማለች)

አሁን መርከቡ የሎረላይን ቋጥኝ እያለፈ ነው። የመርከቡ መሪም ስለ ሎረላይ የሚነገረውን አፈ-ታሪክ ለተሳፋሪዎቹ ይገልጻል።

ሰውዬው አሁን በስተቀኝ የምታዩት ሎረላይን ነው። ቋጥኙን
በደምብ ተመልከቱ! እዚያ ነበረች፣ ሎረላይ! በጣም
ውብ ነበረች። ብዙ፣ ብዙ መርከበኞች አይተዋታል -
እንዴና ለመጨረሻ! ቋጥኙን በትክክል አስተውሉ።
ምናልባት ታይዋት ይሆናል።

ከዚያም አንድሬያስ ጥንት *Heinzelmännchen* እዚያ ሳይኖሩ እንዳልቀሩ ይረዳል። ይህንንም ከኤክስ ለማወቅ ይፈልጋል -ግን በከንቱ!

ሰውዬው ቋጥኙ ውስጥ ጥንት አንድ ዋሻ ይገኝ ነበር። በዚያም
*Heinzelmännchen* ይኖሩ ነበር ነው የሚባለው

አንድሬያስ ኤክስ፣ ይህን ታውቂ ነበር?

ኤክስ (ጉሮሮዋን እንደመጠራረግ ብቻ ትላለች)

አንድሬያስ ኤክስ አንድ ነገር ጠይቄሻለሁ!

ኤክስ (ጉሮሮዋን እንደመጠራረግ ብቻ ትላለች)

አንድሬያስ ቀድሞ እዚያ ነበርሽ? ከዚያ ነው የመጣሽው?
*Heinzelmännchen*-ን ታውቂያለሽ?
(ኤክስ መልስ አትሰጥም)ኤክስ፣ የት ነሽ? ኤክስ አልሰማሽም!
ኤክስ!

ወሮ/በርገር ምን ተፈጠረ?

አንድሬያስ ኤክስ የጠፋች ይመስለኛል